የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.25
ADDIS ABABA 10th March, 2017

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፯/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለሀሙሲት-እስቴ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………ገጽ ፱ሺ፭፻፸፪

Proclamation No. 997/2017

OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Hamusit-Estie Road Project, Ratification Proclamation …….. --Page 9572

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፯/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሀሙሲት-እስቴ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፳ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.አ.አ ኖቬምበር ፱ ቀን ፪ሺ፲፮ በቪየና የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 997/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 20,000,000.00 (Twenty million) United States Dollars for financing the Hamusit-Estie Road Project, was signed in Vienna on the 9th day of November, 2016;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of February, 2017;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለሀሙሲት-እስቴ የመንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፯/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በነዳጅ አምራችና ላኪ አገራት ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.አ.አ ኖቬምበር፱ቀን ፪ሺ፲፮ በቬየና የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2448P በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Hamusit-Estie Road Project, Ratification Proclamation No. 997/2017"

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement No. 2448P signed in Vienna on the 9th day of November, 2016, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 20,000,000.00 (Twenty million) United States Dollars in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done At Addis Ababa, this 10th day of March, 2017.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDANT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**